# ፋኖ ሁን!



የምትኖር ተአገር ውስጥ ተውጪም ተሰደህ፣
ተባዕድ ተሻርከው ዘርህን ሲያጠፉህ፣
ልክ እንደ አያቶችህ ዋሸንት አንቆርቁረህ፣
እንደ አምስቱ ዘመን ፋኖ በል ፎክረህ፡፡

ወገንህ ሲታረድ አድፍጠህ የተኛህ፣
ሆድህን እንደ ኬሻ በእህል እየሞላህ፣
እንኳን ትውልድ ታሪክ እግዜርም አይምርህ፡፡

ወራሪ አንበርክኮ ድንበር በጠበቀ፣
አገርን መስርቶ ኑሩበት ስላለ፣
ባጎረሳቸው እጅ አንገቱ ታረደ፣
አማራ በባትሪ እየተፈለገ፡፡

መነኮሰ ሞተን ተራስህ ላይ ደፍተህ፣
ምእመናን ሲሰው ታርጁ ጋር ቆመህ፣
አትግደል ለማለት ሥጋ እንቅ ታረገህ፣
የጨበጥከው መስቀል እሳት ሆኖ ይፍጅህ፡፡

ዶክተር ፕሮፌሰር ምሁር ሊቅ ነኝ እያልክ፣
በጭራቅ ሲታረድ በመደዳ ሕዝብህ፣
የአማራን ዘር ፍጅት ሙልጭ አርገህ ክደህ፣
የእናቴ መቀነት አደናቅፎኝ እያልክ፣
ድምጥህን አጥፍተህ ቁርጥ መዛቅ የቀጠልክ፣
ተላንቃህ ተጣብቆ እረፍት እንቅልፍ ይንሳህ፡፡

ተአምስቱ ዘመን ጅብ ተሮም የከረፋ፣
ተቱርክ ተላላኪ ተግራኝ የከፋ፣
ማህፀንን ቀዶ ዘርህን የሚያጠፋ፣
ቁማርተኛ መጥቷል ልብ በል አማራ፣
በአገር በውጩ ዓለም ፋኖ ተሰማራ!

በጉርሻ አትንሸንገል እንደ ውሻ ባንዳ፣
አርበኛ ፋኖ ሁን ተዳር ዳር አማራ!

ሺህ አመት ላትኖር ነገ አፈር ልትሆን፣
ለሆድህ ለከርስህ አትሺጥ ህሊናህን፣
ሱሪህን ከፍ አርገህ አጥብቅ ቀበቶህን፣
እንደ ቅደም አያትህ አማራ ፋኖ ሁን፡ ፡

በላይነህ አባተ (Abatebelai@ yahoo.com)
ሚያዚያ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ. ም.